# መተባበር ባንችል እንኳን መሰዳደብ (መዘላለፍ) ብናቆም

መቼም የኢትዮጵያን ፓለቲካና ፖለቲከኞች እንደኔ ከዳር ሆኖ በጥሞና ለሚከታተል ሰው የሀገራችንን ባህልና ወግ ካላወቀ እነዚህ ሰዎች መሰዳደብ መነቋቆር መዘላለፍ ባህላቸው ነው ሳይለን አይቀርም:: አለመታደል ሆኖ አብረን መብላት እንጂ አብሮ መስራት በጣም ያስቸግረናል:: አብሮ መብላትም አሁን አሁን እየቀረ ነው መሰል:: በጋራ የተጀመሩ ብዙ ነገሮችን ስናስተውል መጨረሻቸው መለያየት ነው:: በተለይ አሁን አሁንማ አብረን እንዳንሰራ የተረገምን ይመስል በሁሉም መስክ መለያየት መበታተን መጣላት ከዛም አልፎ አብረን የተጓዝናቸውን ጊዜያት መርገምና አብረውን የሰሩትን ሰዎች ማሽሟጠጥ የተለመደ ሆኗል። በጣም የሚገርመኝ ደግሞ ይህ እየተጠናወተን ያለው ባህል በሁሉም መስኩ መሆኑ ዕውነትም እርግማን ነው እንድል ያስገድደኛል። እስቲ አስቡት በትዳር፣ በጓደኝነት፣ በቢዝነስ፣ በፓለቲካ ድርጅቶች፣ በእምነት ደርጅቶች፣ በስፖርቱ፣ በ … ምን ልበላችሁ በሁሉም መስክ ስታዩት አንድ የነበረው ሁለት፣ ሁለት የነበረው አራት ሲሆን ነው የሚታየው፡፡ በርግጥ የሰው ልጆች የሃሳብ ልዩነት መኖር የነበረ ያለና የሚኖር ሲሆን የሃሳብ ልዩነት መኖር ደግሞ በመነጋገርና በመወያየት ለሚያምን ህብረተሰብ በማንኛውም መስክ የተሻለ ነገር ለመስራትና የበለጠ ነገር ለማምጣት ይረዳል፡፡ የሃሳብ ልዩነትን ደግሞ አቻችሎ መኖር ከአስተዋይ ህብረተሰብ ይጠበቃል:: አሁን አሁን ስናየው ግን በእኛ ህብረተሰብ ውስጥ የሃሳብ ልዩነት የጠላትነት መፈረጃ ቀይ መስመር አድርገነው ከእኛ ሀሳብ ውጭ የሚያራምድን ሰው በሙሉ ጠላት አድርገን እናየዋለን::  ኧረ እስቲ እናስተውል! በዕርግጥ የራዕይ አንድነታችን ወይም የአላማ ግባችን በሰፊው ሲለያዩ አብረን የነበርን ሰዎች ተለያይተን የራሳችንን እምነት ማራመዱ አብረን ሆነን ከመነታረኩ የተሻለ ይሆናል:: ነገር ግን በሆነው ባልሆነው ድሮ ህጻን ሆነን እንደምናደርገው ጨዋታው አለቀ ዳቦው ተቆረሰ ብለን መለያየቱ የአስተሳሰብ ብስለታችንን ከጥያቄ ውስጥ ይከተዋል፣ በተለይ ደግሞ ከተለያየን በኃላ ከእኛ ሀሳብ ውጪ የሚያራምድን ሁሉ የምናይበት መነፅር የጠላትነት መሆኑ ለእኔ በጣም ያስገርመኛል::

ይህን ፅሁፍ ለመፃፍ ወደአነሳሳኝ ዋና ነጥብ ሀሳቤን ትኩረት ልስጠውና እዚህ አሜሪካ መኖር ከጀመርኩኝ አንድ አመት ጀምሮ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ላይ የሚፃፉትን፣ የሚነገሩትን፣ የሚወሩትን አብዛኛውን ለመከታተል ጊዜ ሰጥቼው ነበር:: በዌብ ሳይቶች፣ በቴሌቪዥንና በሬዲዮ የሚቀርቡትን ሀሳቦች ለየትኛውም የተቃዋሚ ድርጅት (ኢትዮጵያ ሆኜ ስሙን ብቻ ከማውቀው ከኢህፓ ጀምሮ በቅርብ እስከማውቀው ቅንጅት ድረስ)

ሳልወግን አደምጥ ነበር::: መቼም የፖለቲካውን በተለይም ደግሞ እዚህ በዳያስፖራው አካባቢ ያለውን እንቅስቃሴ ለተከታተል ሰው ደግሞ በዚህ አንድ አመት ውስጥ ብዙ የተለያዩ ነገሮች ሲከሰት አይተናል:: ልላውን ነገር በቀጠሮ እናቆየውና ለኔ አልገባህ ወዳለኝ ምናልባት ሌሎቻችሁም እንደኔ ግራ ተጋብታችሁበት ሊሆን ወደሚችለው ጉዳይ ትኩረቴን ላድርግ::

በአብዛኛው ኧረ እንደውም በሁሉም ለማለት ሳልገደድ አልቀርም የፖለቲካ ተዋናኞቻችን ውስጥ የሚንፀባረቅ ከኔ ሃሳብ ውጪ ላሳር (my way or no way) የሚል አስተሳሰብ በስፋት ይታያል:: ይቅርታ አድርጉልኝና እንደውም ከፖለቲካ መሪዎችም አልፎ ይኼ ነገር በእኛ በህብረተሰቡ ዘንድም የሚታይ ይመስለኛል:: አብዛኞቹ የፖለቲካ ድርጅቶችና መሪዎች እኛ ያልመራነው ፓለቲካ የትም አይደርስም ሲሉ ይደመጣሉ:: የነሱ አስተሳብና ርዕዮተአለም ብቻ ወደሚፈለገው ግብ እንደሚያደርስ በአፅንኦት ይናገራሉ:: ያም ብቻ ሳይሆን ሌሎች የሚሄዱበት መንገድ በፍፁም ትክክል እንዳልሆነ ያስረዳሉ:: ከዚያም አለፍ ይሉና ከነሱ አስተሳሰብና አሰራር ውጭ የሄዱትን ሰዎች በሙሉ ውጉዝ ከመአርዮስ ብለው እርፍ:: በዛም ቢያርፍ ጥሩ፣ ነገር ግን ህብረተሰቡ እነሱን እንዳያደምጥና እንዳይደግፍ ከደገፈም የኢትዮጵያ ጠላት እንደሆነ መልሰው ለህብረተሰቡ ይነግሩታል:: እንደመለስ ፈራጁም፣ ከሳሹም፣ ዳኛውም፣ ምስክሩም እነሱ ይሆናሉ:: አንዳንዴ ኢትዮጵያ የምትባለው ሃገር የነሱ ብቻ የሆነችም ያስመስሉታል:: ከዛም ይቀጥልና ከነሱ አስተሳሰብ ወይም መንገድ ውጪ የሆኑትን የፖለቲካ ሃይሎች ብቻ ሳይሆን እነሱን የደገፈውንም ሕዝብ ጨምረው ሙልጭ አድርገው ከሰደቡ በኃላ መደምደሚያቸው የወያኔ ቅጥረኛ ወይም ወያኔ ብለው መሰየም ይሆናል:: ጉበዝ! ወያኔ የሚለው ስም ከኛ ሃሳብ ጋር ላልሄደ ሰው ሁሉ የምንሰጠው ስም ከሆነ ፡ አንዳችን ሌላችንን ወያኔ እያልን ሁላችንም ወያኔ እንዳንሆን እሰጋለሁ::

የሚገርመው ሌላው ደግሞ በኢትዮጵያ የፕሬስ ነፃነት አለመኖሩን የሚያስተጋቡት በስደት ላይ ያሉት ሚድያዎችም የዚህ " my way or no way " አስተሳሰብ ሰለባ መሆናቸው ነው:: እነሱ የመሰላቸውን አንዱን የፓለቲካ ድርጅት ይወግኑና ሌላው ላይ የስድብ መአት ሲያወርዱ ይስማሉ:: (በእርግጥ ሁሉም እንዳልሆኑ ይታወቅልኝ)

በመሠረቱ ፕሬስ ነፃ መሆን አለበት:: ከየትኛውም ወገን የመጣን አስተያየት ማስተናገድ ይገባዋልም ብዬ አምናለሁ::

እኔ ግራ የገባኝና በዚህ ፅሁፍ መነሻነት ሁላችንም እንድወያይበት የፈለግኩት ዋና ቁም ነገር እንግዲ ይህ ነው:: ልዩነታችንን አቻችለን አብረን መስራት ባንችል እንኳን በልዩነቶቻችን ተስማምተን ሳንሰዳደብና ሳንጣላ የያዝነው አላማ ለማሳካት ጥረት ብናደርግ

ትርፋችን የተሻለ አይሆንምን? በእኔ እበልጣለሁ ወይም ከእኔ መንገድ ውጪ መንገዶች ሁሉ ወደ ገደል ናቸው ከሚል አስተሳሰብ ወጥተን ሁሉም በመረጠው በአሰበውና ባዋጣው መንገድ ቢታገልና በመጨረሻም የምንፈልገውን ሃገራችን ላይ የተጋረጠውን አደጋ መታደግና ብሎም የተሻለች ሉዓላዊ፣ ዲሞክራሲያዊና ሰላማዊ ኢትዮጵያን ለመገንባት መስራቱ አይሻልምን? ካልተሰዳደብንና የሌሎችን መንገድ ካላጣጣልን መታገል አንችልም? ኧረ እባካችሁ ቆም ብለን እንነጋገር! ከአዲስ አባባ ተነስተን አሰብ ለመሄድ የግድ በናዝሬት አርገን በአዋሽ አቋርጠን በመኪና መሄድ የለብንም:: ከፈለግን በኮምቦልቻ አድርገን በሚሌ በመኪና መሄድ እንችላለን አልያም ደግሞ በአይሮፕላንም መሄድ እንችላለን:: በእርግጥ እያንዳንዱ መንገድ የሚወስድብን ጊዜ፣ ነዳጅና ገንዘብ ሊለያይ ይችላል:: ነገር ግን ሁላችንም በመረጥነው መንገድ መሄድ እንችላለን:: እኔ በዚህኛው መንገድ መሄድ ስለፈለኩ በሌላኛው መንገድ የሄደን ሁሉ የማርያም ጠላት አናድርገው:: ምክንያቱም ሁሉም ሰው እንደእኔ ማሰብ የለበትምና:: የሰው ልጅ የፈለገውን የማሰብና የመረጠውን መንገድ የመከተል መብቱ በተረጋገጠበት በአንደኛው ዓለም እየኖርን የሰውን አዕምሮ በኛ አስተሳሰብ አንምራው:: የራሳችንን ሃሳብ ከማራመድና ያልመሰለንን ነገር በተጨባጭ ማስረጃ አስደግፈን ሂሳዊ አስተያየት ከመስጠት አልፈን የሰውን ስብዕና በሚነካ መልኩ መሳደብ የጨዋ ባህላችንም የምንኖርበት ሃገር ሕገ መንግስትም አይፈቅዱልንምና እባካችሁ መሰዳደብ፣ መነታረክና መቧጨቅ ትተን ለትግሉ ትልቅ ትኩረት እንስጥ:: ለመሳደብ የምናጠፋውን ጊዜና ጉልበት ለትግሉ ጠቀሜታ ያለው ነገር ለማድረግ እናውለው:: ተስማምትን ተግባብተን አብረን መስራት ባንችል እንኳን መሰዳደባችንን እናቁም እላለሁ::

በዚህ ላይ አንድ የመወያያ መድረክ መክፈት ለሚችሉ ደግሞ እባካችሁ እያልኩ ጥያቄዬን አቀርባለሁ::

አምላክ እምዬ ኢትዮጵያን ከገባችበት መቅሰፍት ያውጣት::

እኛንም ከገባንበት 'የኔ ብቻ አስተሳሰብ" ያላቀን::

Lehagere

lehagere@yahoo.com